አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

# **<u>የውሃ ቆጣቢ እቃዎች አጠቃቀም መመሪያ 13/2012</u>**

## መግቢያ

ባለስልጣኑ ለከተማው ነዋሪ የሚያቀርበውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ጥራትና መጠን በማሳደግ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ስርጭቱን ለማስፋት እና ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ በመሆኑ፡፡

ይህም አላማ ግቡን ይመታ ዘንድ በስርጭት እና በአጠቃቀም ካላግባብ የሚባክነውን የውሃ መጠን መቀነሱ የውሃ ስርጭት የአቅርቦቱን መጠን ለመጨመር የሚረዳ በመሆኑና ደንበኞች በተለይም ትላልቅ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች ውስን የሆነውን የውሃ ሀብት በአግባቡ የማይጠቀሙ በመሆኑና በዚህም የውሃ እጥረት እየገጠመ መሆኑ ደንበኞች ውሃ የማያበክኑ እና ውሃ ቆጣቢ እቃዎችን እንዲጠቀሙ ማድረጉ በአጠቃቀም ወቅት አላግባብ የሚባክነውን ውሃ መጠን ለመቀነስና የውሃ ስርጭቱን ፍትሃዊ እና ተደራሽ ለማመድረግ የሚረዳ በመሆኑ፡፡

በአጠቃቀም ምክንያት አላግባብ የሚባክነውን ውሃ ለመቀነስ ደምበኞች የውሃ ቆጣቢ እና ውሃን ከብክነት የሚከላከሉ እቃዎችን እንዲጠቀሙ ለማድረግ የሚረዳ የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት በማስፈለጉ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ
### አንቀፅ አንድ
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን የውሃ ቆጣቢ እቃዎች አጠቃቀም መመሪያ 13/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽሁለት
### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ

1. **"ባለሥልጣን"** ማለት ፡-የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችንም ያጠቃልላል፡፡
2. **"ዋና ሥራ አስኪያጅ"** ማለት፡- የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፡፡
3. **"ዘርፍ ማለት"** ፡-፡-የባለስልጣኑ የውሃ አገልግሎት ም/ዋ/ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡
4. **"የውሃ ምርት "** ማለት ፡-ባለስልጣኑ ከገጸ ምድር እና ከርሰ ምድር የውሃ መገኛዎቹ ያገኛኘውና የአለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት መሰረት ተጣርቶና ታክሞ የቀረበ ለጤና ተስማሚ የሆነ ንፁህ ውሃ ነው፡፡
5. **"ገጸ-ምድር የውሃ መገኛ"** ማለት፡-ከዝናብ እና ከጎርፍ በግድብ አማካኝነት የተሰበሰበው ጥሬ ውሃ የሚከማማችበት እና እየተመረተ ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭ ማለት ነው፡፡
6. **"ከርሰ ምድር"**ማለት፡-ከጥልቅ ጉድጓድ ተቆፍሮ በማውጣት ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭ ውሃ ማለት ነው፡፡
7. **"የውሃ ማጣሪያ ጣቢያ"**ማለት፡-ማለት ፡- የአለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት መሰረት የገጸ ምድር ውሃ ክምችት የሚጣራበት ቦታ ነው፡፡
8. **"የውሃስርጭት"**ማለት ማለት ፡-ከየውሃ ምርት መገኛ ጣቢያዎች የሚገኙትን የውሃ ምርቶች ማሰራጨት ማለት ነው፡፡
9. **"ማጠራቀሚያ"**ማለት ፡-እንደቃሉ አገባብ ባለስልጣኑ በከተማው ውስጥ በተለያየ ቦታ ከምርት ጣቢያ የሚመጣውን የተጣራ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያከማችበት ማጠራቀሚያ ወይም ደንበኞች በግቢያቸው ወይም በየቦታቸው ውስጥ ከባለስልጣኑ የሚቀርብላቸውን የተጣራ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያከማቹበት የውሃ ማጠራቀሚያ ነው፡፡
10. **"ሰራተኛ" ማለት**፡-በባለስልጣኑ ለተወሰነም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛ ማለት ነው፡፡
11. **"ደንበኛ"** ማለት፡-ከባለስልጣኑ ጋር የውሃ አገልግሎት ለማግኘት ውል የፈፀመ ማናቸውም ሰው ማለት ነው፡፡
12. **"ዋና ዋና ደንበኞች" ማለት**፡--ከባለስልጣኑ ጋር የውሃ አገልግሎት ለማግኘት ውል የፈፀመ ማናቸውም ሰው ሆኖ የሚጠቀመው የውሃ መጠን ከ500 ሜ/ኪ. በላይ የሆነ ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ ሦስት
## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም ደረጃ ላይ ባሉ የባለስልጣኑ የሥራ መሪዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም ከባለስልጣኑ የውሃ አገልግሎት በሚያገኙ ደንበኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ተግባር፣ ኃላፊነትና ግዴታዎች
## አንቀፅ አራት
## የትምህርትና ስልጣና ተቋም ተግባርና ሀላፊነት

1. የውሃ መገኛዎች፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎች፣የግፊት መስጫ ጣቢያ፣ የውሃ ብክነትና ብክለት መከላከል ስልትን ለሚመለከታቸው ሰራተኞችና ደንበኞች ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት አለበት፡፡
2. በየበጀት አመቱ እቅድ በማዘጋጀት ለደንበኞች ስለ ውሃ አጠቃቀም፤ቁጠባ እና አያያዝ ስልጠና ይሰጣል፡፡
3. ለደንበኞች በተለይ ለዋና ዋና የውሃ ተጠቃሚዎች በየጊዜው ክትትል በማድረግ የውሃ አጠቃቀማቸውን መረጃ በመሰብሰብ የውሃ ቆጣቢ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ የተለያዩ መሳሪያዎችን ማሳየት እና ግንዛቤ መስጠት አለበት፡፡
4. በየስራ ክፍሉ ለተመደቡ ነባርና አዳዲስ ሠራተኞች የብክነት መፈለጊያ መሣሪያዎች ሥልጠና መስጠትና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ ይኖርበታል፡፡
5. ዘመኑ የደረሰበትን ወቅታዊ የውሃ ብክነትና ብክለት መከታተያና መከላከያ ቴክኖሎጂ እና ውሃ ቆጣቢ መሳሪያዎችን አቅም ባገናዘበ መልኩ ተገዝተው ስራ ላይ እንዲውሉ የመሳሪያውን ጠቀሜታ ለባለስልጣኑ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት ፡፡
6. ከውሃ ማምረት ጀምሮ እስከ ተጠቃሚው ድረስ ያለውን የውሃ ስርጭት ሁኔታ ለህብረተሰቡ ስልጠና በመስጠት የውሃ አጠቃቀማቸውን እንዲያስተካክሉ ግንዛቤ መስጠት አለበት፡፡

## አንቀጽ አምስት
## ደንበኛ(ኞች) ግዴታ

1. የውሃ ማጠራቀሚያ የሚጠቀምበት እቃ ከመሬት በላይ በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

2. የውሃ ማጠራቀሚያው የተቀደደ፤የተበሳ፤የተሰነጠቀ እና የሚያንጠባጥብ ከሆነ ወዲያውኑ የማስጠገን ወይም የመለወጥ ግዴታ አለበት፡፡
3. ወደ ውሃ ማጠራቀሚያ የሚገባው መስመር በራሱ የሚዘጋ እና የሚከፍት የውሃ መክፈቻ እና መዝጊያ ያለው ውሃ ቆጣቢ እቃ መጠቀም ግዴታ አለበት፡፡
4. በፋብሪካ ፣በተቋም ፣በትምህርት ቤት ፣በሆቴል ፣በንግድ ተቋማት እና በመኖሪያ ቤት ውስጥ ለምርት ፣ ለመፀዳጃ ቤት፤ለንፅህና መጠበቂያ፤ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀምበትን ውሃ በቁጠባ እና በአግባቡ የመጠቀም እንዲሁም የውሃ ቆጣቢ እቃዎችን የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ ስድስት
### ተጠያቂነት

1. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጣለበትን ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጣ የሥራ መሪ / ሰራተኛ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብና በህብረት ስምምነት መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ያደናቀፈ ወይም ትርጉሙን እና አሰራሩን ያዛባ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊና ሰራተኛ በፍ/ብሔርና የወንጀል ህግ ያለው ተጠያቂነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በህብረት ስምምነቱ እና በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተገቢው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡
3. የውሃ ማጠራቀሚያውን ከመሬት በታች ያስቀመጠ፤ውሃን ለማጠራቀም የሚያፈስ የውሃ ማጠራቀሚያ የተጠቀመ ደንበኛ ለባከነው ውሃ የፍ/ሃብሔር ተጠያቂነት እና አግባብ ባለው የባለስልጣኑ ደንብ መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለስልጣኑ ለደንበኛው የሚሰጠውን የውሃ አገልግሎት ለተወሰነ ግዜ ለማቋረጥ ይችላል ፡፡
4. በዚህ መመሪያ መሰረት ያለበትን ክልከላ የተላለፈ ፣ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣ ያሳሳተ ወይም የሐሰት መረጃ የሰጠ ደንበኛ አግባብ ባለው የሀገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለስልጣኑ ለደንበኛው የሚሰጠውን የውሃ አገልግሎት ለተወሰነ ግዜ ለማቋረጥ ይችላል ፡፡

### አንቀጽ ሰባት

### ክልከላ

1. ውሃን የሚያንጠባጥብ ፣የሚያፈስ እንዲሁም ውሃን የሚያባክን ዕቃ እና የውሃ ማጠራቀሚያ መጠቀም የተከለከለ ነው፡
2. የውሃ ማጠራቀሚያ ከመሬት በታች ቆፍሮ ማስቀመጥ ወይም በመሬት ውስጥ በተቀበረ የውሃ ማጠራቀሚያ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀፅ ስምንት

## መመሪያውን የማሳወቅ ግዴታ

የባለስልጣኑ የትምህርትና ስልጣና ተቋም የባለስልጣኑ የሥራ ሃላፊዎች፣ ሰራተኞች ፣ ደንበኞች እና የሚመለከታቸው አካላት ስለ አሰራሩ እና ስለመመሪያው አፈፃፀም በቂ እውቀት እንዲኖራቸው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀፅ ዘጠኝ

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## አንቀፅ አስር

## የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በየትኛውም ደረጃ ያሉ የባለስልጣኑ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች ፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ህግና ደንብ እንዲያስከብሩ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ማንኛውም ሰው እና ደንበኞች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ አስራ አንድ

## ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ወይም አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀፅ አስራ ሁለት

## መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተፈርሞና የባለሥልጣኑ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አወቀ ኃይለማርያም**

**የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን**

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**